
በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ
በሰ/ወሎ አስተዳደር ዞን የአቡነ ዮሴፍ፣ ዝጊትና አቦይ ጋራ ተራራዎች የማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራን ህጋዊ ዕውቅና ለማስጠት የተዘጋጀ ደጋፊ ሰነድ
የዱር እንስሳት ጥናት፣ ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ዋና የስራ ሂደት
የካቲት/2006 ዓ.ም
ባ/ዳር

ማውጫ

1. መግቢያ 1
1.1. አጠቃላይ ሁኔታ 1
2. የደጋፊ ሰነዱ ዓላማዎች 2
2.1. አጠቃላይ ዓላማ 2
2.2. ዝርዝር ዓላማዎች 2
3. የአየር ንብረትና መገኛ 2
3.1. መገኛና ስፋት 2
3.2. አግሮ ኢኮሎጂና የአየር ንብረት፣ 4
4. ብዝሐ ህይወትና ብርቅይነት 4
4.1. አጥቢ እንስሳት 4
4.2. አእዋፋት 5
4.3. የእፅዋት ሽፋንና ዓይነት 6
5. በተፈጥሮ ሃብቱ አካባቢ ያሉ ታሪካዊ፣ ባህላዊና ኃይማኖታዊ የቱሪዝም ሃብቶች ሁኔታ 7
6. በታሳቢ የማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራው የሚኖሩ ህዝቦች አኗኗርና የሚያደርሱት ተፅዕኖ 8
6.1. የአካባቢው ነዋሪዎች ሁኔታ 8
6.2. በተፈጥሮ አካባቢው ላይ የሚታዩ ጫናዎች/ተጽዕኖዎች 9
7. የማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራው የሚኖረው ጠቀሜታ 11
8. የማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራው የወደፊት የጥበቃ ሁኔታ 13
9. ማጠቃለያ 13
ዕዝል1- የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው ወሰን ዝርዝር መግለጫ 16
ዕዝል- 2 የአቡነ ዮሴፍ፣ ዝጊትና አቦይ ጋራ ተራራዎች …. ጥብቅ ስፍራ የክለላ ካርታ 24
ዕዝል-3 የፀደቀ የቀበሌ ቃለጉባኤ (ናሙና ቀበሌ፡ ሐዋርያው ጴጥሮስ) 25
ዕዝል-4 የጸደቀ የወረዳ ቃለ ጉባኤ (ናሙና ወረዳ: ጋዘጊብላ) 27

1. መግቢያ

1.1. አጠቃላይ ሁኔታ

ከሰሃራ በታች ከ3200 ሜትር ከፍታ በላይ ከሚገኙ አጠቃላይ ውርጭና ውርጭ ቀመስ ሥርዓተ ምህዳሮች (Afroalpine and Sub-afroalpine Ecosystems) /11887 ካ.ኪ.ሜ/ ውስጥ ኢትዮጵያ 73% (8677 ካ.ኪ.ሜ) የሚሆነውን ድርሻ ይዛ ትገኛለች፡፡ ከዚህም ውስጥ 83% (7220 ካ.ኪ.ሜ) የሚሆነው የሚገኘው በሀገሪቱ በሚገኙ 9 የተራራ ሰንሰለቶች ነው፡፡ በውርጭና ውርጭ ቀመስ ሥርዓተ ምህዳሮች (Afroalpine and sub-afroalpine Ecosystems) ከሚታወቁት 9 የተራራ ሰንሰለቶች ውስጥ ሰባቱ በአማራ ክልል በ6 ዞኖች (በምስራቅ ጎጃም፣ ሰሜን ጎንደር፣ ደቡብ ጎንደር፣ ደቡብ ወሎ፣ ሰሜን ወሎና ሰሜን ሸዋ) የሚገኙ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ አምስቱ በሀገራችን ብቻ የሚገኘው የቀይ ቀበሮ መኖሪያ ናቸው፡፡

በሰሜን ወሎ ዞን የሚገኙት የአቡነ ዮሴፍና አቦይ ጋራ ተራራዎች ሰንሰለት የቀይ ቀበሮ መጠለያ ከሆኑት አምስት የተራራ ሰንሰለቶች ውስጥ አንዱ ሲሆን የበርካታ ብዝሐ ህይወት መጠለያና የተከዜ ተፋሰስ የውኃ ማማ በመሆኑ ለተፋሰሱ ገባር የሆኑ ድንበር ተሻጋሪ ወንዞች /የ20 ወንዞችና በርካታ ምንጮች/ መነሻ ነው፡፡

በሀገራችን የሚገኙት የውርጭና ውርጭ ቀመስ ስርዓተ ምህዳሮች የብዝሐ ህይወት ክምችት ቁልፍ ቦታዎች ከመሆናቸውም ባሻገር የምስራቅ አፍሪካ የውኃ ማማዎች ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ ስርዓተ ምህዳሮች (ውርጭና ውርጭ ቀመስ) በእርሻ መስፋፋት፣ በህገ ወጥ መንደር ምስረታ፣ በልቅ ግጦሽ እና ደን ጭፍጨፋ ምክንያት ከፍተኛ ጉዳት እየደረሰባቸው ይገኛል፡፡

በተለይም በከፍተኛ ተጽእኖ ውስጥ የሚገኘውና ምንም ዓይነት የአጠቃቀምና አጠባበቅ ስርዓት የሌለውን የአቡነ ዮሴፍ፣ አቦይ ጋራ ተራራዎችና አካባቢውን ከጥፋት ለመታደግ እንዲሁም የአካባቢውን ማኅበረሰብ በዘላቂነት ተጠቃሚ ለማድረግ እንዲቻል ቢሮው ከፍራክፈርት ዞሎጂካል ሶሳይቲ ጋር በመቀናጀት በ2005 ዓ.ም መሰረታዊ የብዝሐ ህይወትና ማኅበረ ኢኮኖሚ የዳሰሳ ጥናትና አሳታፊ የእምብርት ዞን ዳር ድንበር ክለላ አካሄዷል፡፡ በተጨማሪም ከጥናትና ክለላ ሪፖርቶች በመነሳት ረቂቅ ደንብ አዘጋጅቶ የባለድርሻ አካላትና የማኅበረሰቡ ተወካዮች በተገኙበት አውደ ጥናት በላሊበላና ሙጃ ከተማዎች ላይ በማካሄድ የተሰጡትን

አስተያየቶችን በማካተት ረቂቅ ደንቡን ለማበልጸግ ተሞክሯል ። ስለሆነም አሳታፊ የዳር ድንበር ክለላ የተከናወናለትን የእምብርት ዞን በህግ ለመደገፍና የማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራውን በዘላቂነት ጥበቃና አጠቃቀሙን የሚከታተል አካል ማቋቋም አስፈላጊ በመሆኑ ለውሳኔ ሰጭ አካላት እንዲረዳ ይህ ደጋፊ ሰነድ ተዘጋጅቷል።

2. የደጋፊ ሰነዱ ዓላማዎች

2.1. አጠቃላይ ዓላማ

በአቡነ ዮሴፍ፣ ዝጊትና አቦይ ጋራ ተራራዎች ታሳቢ የማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራ እስከአሁን የተጠኑ ጥናቶችንና የእምብርት ዞን ዳር ድንበር ክለላን መነሻ በማድረግ በታሳቢ ማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራው ውስጥ ያለውን ሃብት በዘላቂነት መጠበቅ እንዲቻል ቦታው የማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራነት ደረጃ የሚያገኝበትን ህጋዊ እውቅና ለማሰጠት አስፈላጊ የሆኑ መሰረታዊ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ መተንተንና ማደራጀት።

2.2. ዝርዝር ዓላማዎች

- የማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራውን ዋና ዋና የዱር እንስሳትና ዕጽዋት ሃብት፣ የመሬት አቀማመጥ፣ የአየር ንብረት መረጃ አጠቃሎ ለማቅረብ፣
- ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ኢኮሎጂያዊ ሁኔታዎችን ከአሁን በፊት የተካሄዱ ጥናቶችን መነሻ በማድረግ ለማደራጀት፣
- የተጠቃለለውን አሳታፊ የእምብርት ዞን የዳር ድንበር ክለላ ሪፖርትና የአካባቢው ማኅበረሰብና ባለድርሻ አካላት የተስማሙበትን ረቂቅ ደንብ በግብዓትነት በመጠቀም አደራጅቶ ለውሳኔ ሰጭ አካላት ማመቻቸት፣

3. የአየር ንብረትና መገኛ

3.1. መገኛና ስፋት

ጥናትና ክለላ የተካሄደባቸው የተፈጥሮ ቦታዎች፣ ከላል ይበላ ከተማ በስተ ሰሜን አቅጣጫ ከ42 እስከ 70ኪ.ሜ ድረስ በሚርቁት የአቡነ ዮሴፍና የአቦይ ጋራ ተራሮች ላይ ያሉ ከፍተኛ ቦታዎች ናቸው።

የማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራው ሁለት የተለያዩ ጥብቅ ስፍራዎችን የያዘ ሲሆን በአጠቃላይ የማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራው ከሁለት ዞኖች፣ ሶስት ወረዳዎችና አስራ አምስት የገጠር ቀበሌዎች ጋር የሚዋሰን ሆኖ በአንድ ጽ/ቤትና በሁለት የተለያዩ የልማትና ጥበቃ ምክር ቤቶች የሚተዳደር በድምሩ 8059 ሄ/ር ስፋት ይኖረዋል፣

የማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራው አንዱ ክፍል የሆነው የአቡነ ዮሴፍ ተራራ ከባህር ወለል ከ3505 እስከ 4280 ሜትር ከፍታ ርቆ፣ ከ$12^0$04’45.13’’ እስከ $12^0$10’11.46’’ ኬክሮስ እና $39^0$08’24.89’’ እስከ $39^0$16’45.46” ኬንትሮስ መስመር ላይ ይገኛል። 5,332 ሄክታር ስፋት ያለው ይህ ከፍተኛ ቦታ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በሰሜን ወሎና ዋግ ኽምራ ብሄረሰብ ዞን ውስጥ ያሉ 8 ቀበሌዎችን ያካልላል። ከዚህ ውስጥ 64 እና 28.4 በመቶ የሚሆነው ቦታ እንደ ቅደም ተከተሉ በሰሜን ወሎ ዞን ስር ባሉት የላስታና ግዳን ወረዳ ሰባት ቀበሌዎች ውስጥ ይገኛል። ቀሪው 7.6 በመቶ ቦታ በዋግ ኽምራ ብሄረሰብ አስተዳደር ዞን ስር ባለው ጋዝ ጊብላ ወረዳ ውስጥ ይገኛል።

የአቡነ ዮሴፍና ዝጊት ተራራ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራ በሰሜን ወሎ አስተዳደር ዞን በላስታና ግዳን ወረዳዎች በ7 ቀበሌዎች እና በዋግኽምራ ብሄረሰብ ዞን ጋዝጊብላ ወረዳ በ1 ቀበሌ የሚገኝና ስፋቱም 5332 ሄ/ር ሲሆን የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው በምዕራብና ሰሜን ከላስታ ወረዳ 016/አቡነ ዮሴፍ/፣ 017/እንጃፋት/፣ 014/ጠልፈጢት/ና 015/ወደብየ ቀበሌዎች፤ በምስራቅና ደቡብ ምስራቅ ከግዳን ወረዳ 022/አጢማጣ/፣ 07/ቀይ ገደል/ና 04/መስቀለሳስ/ ቀበሌዎች እንዲሁም በሰሜን ምዕራብ ከጋዝጊብላ ወረዳ ሐዋርያው ጴጥሮስ ቀበሌ ጋር ይዋሰናል፣

በአቦይ ጋራ ላይ የማኅበረሰብ ጥብቅ ቦታ እንዲሆን የተመረጠው አካባቢ ከአቡነ ዮሴፍ ተራራ በስተ ሰሜን አቅጣጫ 8.4 ኪ.ሜ ይርቃል። ከባህር ወለል ከ3505 እስከ 4280 ሜትር ከፍታን የሚሸፍነው ይህ ታሳቢ ጥብቅ ቦታ ከ$12^0$06’13.04’’ እስከ $12^0$0248.05’’ ምስራቅ ኬክሮስ እና ከ$39^0$23’35.75’’ እስከ 39^0 21’09.24”ሰሜን ኬንትሮስ መስመር ላይ ይገኛል።

የአቦይ ጋራ ተራራ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራ በግዳን ወረዳ በ7 አዋሳኝ ቀበሌዎች የሚገኝና ስፋቱም 2727 ሄ/ር ሲሆን የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው በሰሜን 030/ወፍጫት/ና

019/አሸኳና/፤ በምዕራብ 03/ወርቅ አወጡ/ና 06/ደንገልሳ/፤ በምስራቅ 014/ጌስታ/ እንዲሁም በደቡብ 018/ቱባ/ና 015/ በቅሎ ማነቂያ/ ጋር ይዋሰናል፡፡

3.2. አግሮ ኢኮሎጂና የአየር ንብረት፣

የአቡነ ዮሴፍ ተራራና አቦይ ጋራ ውርጭና ቁር በሚበዛበት አግሮ ኢኮሎጂ ቀጠና ይገኛሉ (ሁርኒ እ.ኤ.አ1998)፡፡ ከፍተኛ እርጥበታማ የአየር ንብረት ባላቸው በነዚህ አካባቢዎች ከሰኔ እስከ መስከረም አጋማሽ ያለው ጊዜ የዝናብ ወቅት ነው፡፡ ከመስከረም አጋማሽ እስከ ግንቦት መጨረሻ ያለው ቀሪ ወራት የበጋ ወቅት ነው፡፡ በዚህ ረጅም የበጋ ወቅት፣ አልፎ አልፎ አነስተኛ የሆነ ዝናብ ለጥቂት ቀናቶች ያገኛል፡፡ ይሁን እንጂ የጥናት አካባቢዎቹ በዋነኛው የክረምት ወቅት ብቻ በዓመት ከ1400 - 2,000 ሚ.ሜ ያላነሰ ዝናብ ያገኛሉ (ፍራንክፈርት ዚኦሎጂ፡ እ.አ.አ 2012)፡፡

4. ብዝሐ ህይወትና ብርቅይነት

ቢሮው ከፍራንክፈርት ዞሎሎጅካል ሶሳይቲ ጋር በመቀናጀት በ2005 ዓ.ም. ባደረገው የዳሰሳ ጥናት መሰረት በአቡነ ዮሴፍና አቦይ ጋራ ተራራዎችና አካባቢው የሚገኘውን ብዝሐ ህይወትና ብርቅይነት በሚመለከት እንደሚከተለው ያብራራዋል፡፡

4.1. አጥቢ እንስሳት

የውርጭና ውርጭ ቀመስ ስርዓተ ምህዳር አካል በሆኑት የአቡነ ዮሴፍና አቦይ ጋራ ተራራ ሰንሰለቶች የሚኖሩ 43 የተለያዩ የአጥቢ ዝርያዎች የተለዩ ሲሆን ይህም በየብስ ከሚኖሩትና በኢትዮጵያ ከሚገኙት ውስጥ 16% ዝርያዎችን የያዘ መሆኑን ያረጋግጥልናል፡፡

በተጨማሪም በኢትዮጵያና ኤርትራ ብቻ ከሚገኙት 31 የአጥቢ እንስሳት ዝርያዎች ውስጥ 8ቱ ብርቅየ ዝርያዎች (25.8% የሚሆኑት) በቦታው ይገኛሉ፡፡ በተለይም በሀገራችን ብቻ ከሚገኙ ከታላላቅ አጥቢዎች መካከልም ህልውናቸው በእንክብካቤ ላይ ከተመሰረቱት (Conservation Dependant) ውስጥ የጭላዳ ዝንጀሮ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ለእልቂት የተቃረበው (Globally Endangered) ቀይ ቀበሮ ይገኙበታል፡፡

4.2. አእዋፋት

በአገራችን ከሚገኙ 864 የአእዋፋት ዝርያዎች ውስጥ 221 (24%) አእዋፋት በዚህ አካባቢ የተለዩ ሲሆን፣ በሀገራችን ብቻ ከሚገኙት 18 ብርቅየ የአእዋፋት ዝርያዎች ውስጥ 6ቱ /35%/ እና ሀገራችን ከኤርትራ ጋር ከምትጋራቸው 13 ብርቅየዎች ውስጥም 8ቱ በእነዚህ አካባቢዎች የሚኖሩ ናቸው።

በተጨማሪም የዓለም አቀፍ የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ ማኅበር /IUCN/ በአዘጋጀው ቀይ የዝርዝር መዝገብ /Red Data Book/ መሰረት በኢትዮጵያ 36 አእዋፋት ዝርያዎች በእልቂት ስጋት ደረጃ ያሉ ሲሆን እነዚህም 2 ለእልቂት የተቃረቡ/Endangered/፣14 ለእልቂት የሚያበቁ ሁኔታዎች ካልተገደቡ ለእልቂት ከተቃረቡት ምድብ የሚሸጋገሩ/Vulnerable/፣16 ለእልቂት ስጋት የተቃረቡ/ Near Threatened/ና 4 የመረጃ አጥረት ያለበት/Data Deficient/ ናቸው። ከዚህም ውስጥ በአቡነ ዮሴፍና አቦይ ጋራ የተራራ ሰንሰለቶችና አካባቢው 9 (25% ከሀገሪቱ) አእዋፋት ዝርያዎች በእልቂት ስጋት ደረጃ ያሉ ሲሆን እነዚህም፡-

- 1 ለእልቂት የተቃረበ/Endangered/፣
    - Ankober serin (*Serinus ankoberensis*)
- 3 ለእልቂት የሚያበቁ/የሚያደርሱ ሁኔታዎች ካልተገደቡ ለእልቂት ከተቃረቡት ምድብ የሚሸጋገሩ/Vulnerable/፣
    - Great spotted eagle (*Aquila clanga*)
    - Lesser kestrel (*Falco naumanni*)
    - Lappet-faced vulture *(Torgos tracheliotus)*
- 4 ለእልቂት ስጋት የተቃረቡ/Near Threatened/
    - Abyssinian longclaw (*Macronyx flavicollis*)
    - Blue-winged goose (*Cyanochen cyanopterus*)
    - White collared pigeon (*Columba albitorques*)
    - Pallid harrier (*Circus macrourus*)

- 1 የመረጃ አጥረት ያለበት/ Data Deficient/

    - Sombre rock chat *(Cercomela dubia)* ይገኙበታል (saavedra *et al*., 2009)።

የአቡነ ዮሴፍና አካባቢው በመካከለኛው የኢትዮጵያ ከፍተኛ ቦታዎች/Central Ethiopian Highlands/ ብቻ ተጠልለው ከሚኖሩት 3 የአእዋፋት ዝርያዎች መካከል 2ቱ ይገኙበታል፡፡ እነዚህም

- Rüeppell´s chat *(Myrmecocichla melaena)*
- Ankober serin *(Serinus ankoberensis)* ናቸው፡፡

ከዚህም ሌላ በአቡነ ዮሴፍ ተራራና አካባቢው ከተመዘገቡት 221 ዝርያዎች በአፍሮ ትሮፒካል ሃይላድ ባዮም ክልል ውስጥ ብቻ (Afrotropical Highland Biome restricted species) ከሚገኙት 49 ዝርያዎች (7ቱ ብርቅየ) ውስጥ ለ36ቱ (75% ለሚሆኑት) የአእዋፋት ዝርያዎች መጠለያ ሲሆን በሀገራችን ብቻ ከሚገኙትና በዓለም አቀፍ ደረጃ ለእልቂት ከተቃረቡ (globally threathened) አዕዋፋት ዝርያዎች መካከል አንዱ Ankober serin(Carduelis ankoberensis) ይገኝበታል:: ይህም ሲታይ በአእዋፋት ዝርያዎች ስብስብ ከባሌ ብሔራዊ ፓርክ (88% ከያዘው) በመቀጠል ከሀገራችን የሁለተኛን ደረጃ ይዞ የሚገኝ በመሆኑ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት በማህበረሰብ ጥብቅ ቦታነት ሕጋዊ እውቅና አግኝቶ ሊጠበቅ ይገባል (saavedra *et al*., 2009)፡፡ በዚህ መሰረትም ከአዕዋፍት ጥበቃ አንፃር ታሳቢ ጥብቅ ስፍራውና አካባቢው በአይ ቢ ኤ መስፈርት (IBA/Important Bird Area/ Criteria) መሰረት ኤ ደረጃ 1፣ ኤ ደረጃ 2 እና ኤ ደረጃ 3 (A1, A2 and A3)[1] እንደሚያሟላ ታውቋል፡፡

4.3. የእፅዋት ሽፋንና ዓይነት

የአቡነ ዮሴፍና አቦይ ጋራ ተራራ ሰንሰለቶችና አካባቢው ከ92 በላይ የሚሆኑ የዕፅዋት ዝርያዎችን የያዘ የተፈጥሮ አካባቢ ነው፡፡ ይህ አካባቢ በዋናነት የውርጭና ውርጭ ቀመስ ስርዓተ ምህዳሮችን ተከትሎ የአስታ፣ ጀበራ፣ የዋልያ እሾህ፣ ጓሳ፣ ጭማ፣ አምጃ፣ ኮሶ፣ ቀጋና አሸንዳ ዕፅዋትን አቅፎ የያዘ ሲሆን በደረቅ ተራራዎች ደንና ቅጠላቸው የማይረግፍ ቁጥቋጦዎች (Dry Evergreen Montane Forest Ecosystem) ሥርዓተ ምህዳር ደግሞ ቅጠላቸው ከማይረግፉ የዛፍና ቁጥቋጦ ዝርያዎች መካከል እንደ የሀበሻ ጽድ፣ ወይራ፣ ኮሶ፣ ክትክታ፣ ደደሆንና ሌሎች ዝርያዎችን ያካትታል፡፡

1 A1= Globally threatened species, A2= Restricted-range/ Endemic species, A3= Biome-Restricted species (Global IBA Criteria).

የጉና ተራራ ሰንሰለትና አካባቢው ከላይ በተጠቀሱት ሥርዓተ ምህዳሮች ብዛት ያላቸው ለመጥፋት የተቃረቡና ዝርያቸው በመመናመን ላይ የሚገኙ ሀገር በቀል ዛፎችን የያዘ ከመሆኑም በላይ በተለይም በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ 5 ዝርያዎችን፡-

- *Acanthus sennii /ኮሸሸላ/*
- *Echinops ellenbeckii/*ኩሸሌ/
- *Kniphofia foliosa/*አሸንዳ/
- *Lobelia rhynchopetalum/*ጅብራ/ጀበራ/
- *Euryops pinifolius/*ጭፍራ/ጨረንፌ

የያዘ ስለሆነ አካባቢው የሚጠበቅበትን ሁኔታ ማመቻቸትና ለጥፋት ተጋላጭ የሆነውን የውርጭና ውርጭ ቀመስ ስርዓተ ምህዳር ማልማትና መንከባከብ ያስፈልጋል፡፡

5. በተፈጥሮ ሃብቱ አካባቢ ያሉ ታሪካዊ፣ ባህላዊና ኃይማኖታዊ የቱሪዝም ሃብቶች ሁኔታ

በአቡነ ዮሴፍና አቦይ ጋራ ተራራ ሰንሰለቶች ዙሪያ የሚገኙ ኃይማኖታዊና ታሪካዊ ቅርሶች በታሳቢ ማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራው ውስጥ ካሉ የተፈጥሮ ሃብቶች እንዲሁም ከቦታው ማራኪ ገጽታ ጋር በማስተሳሰር ወደ ልማት ገብተው የቱሪስት መዳረሻ መሆን ቢችሉ በሚኖረው የቱሪዝም እንቅስቃሴ ምክንያት ለክልሉም ሆነ ለአካባቢው ማኅበረሰብ ከፍተኛ የሆነ የማኅበረ ኢኮኖሚ አስተዋጾ ማበርከት ይችላሉ፡፡ ከእነዚህ ቅርሶች ውስጥ በከፊል የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል፡-

በአቡነ ዮሴፍና አቦይ ጋራ ተራራዎች ዙሪያ

- ከቦታው ትውፊታዊ አጠባበቅ ጋር የተቆራኘው የአቡነ ዮሴፍ ፍልፍል ቤተክርስቲያን
- ዓለምን የሚያሰደምሙትና በ12ኛው ክፍለ ዘመን ላይ ከዛግዌ ስርወ መንግሥት አንዱ በሆነው ንጉስ ላል ይበላ የተገነቡት የቅዱስ ላል ይበላ 11ዱ ውቅር አብያተክርስቲያናት፣
- የይምርሀነ ክርስቶስ ፍልፍል ቤተክርስቲያን፣
- የነአኩቶለአብና የአሸተን ማርያም ፍልፍል አብያተክርስቲያናት ይገኛሉ፡፡

- ከእነዚህ ታሪካዊና ሐይማኖታዊ ቅርሶች ጎን ለጎን በ5ኛውና በ6ኛው ክፍለ ዘመን በአፄ ካሌብና በአፄ ኢያሱ የተገነቡት የገነተ ማርያም፣ የብልባላ ጊዮርጊስና የአርባዕቱ እንስሳ ፍልፍል አብያተክርስቲያናት በአሁኑ ወቅት የበርካታ ቱሪስቶች መዳረሻዎች ናቸው።

6. በታሳቢ የማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራው የሚኖሩ ህዝቦች አኗኗርና የሚያደርሱት ተፅዕኖ

6.1. የአካባቢው ነዋሪዎች ሁኔታ

በ2002 ዓ.ም አገር አቀፍ የህዝብና ቤት ቆጠራ ውጤት መሰረት፣ በአሁኑ ወቅት የአቡነ ዮሴፍ፣ ዝጊትና አቦይ ጋራ ተራራዎች ታሳቢ ማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራ አዋሳኝ በሆኑት 15 ቀበሌዎች ከ91,317 ያላነሰ ህዝብ (45,203 ወንድና 46,114 ሴቶች) ይኖራሉ። ይህ ታሳቢ የማህበረሰብ ጥብቅ ቦታ በሚያካልላቸው ቀበሌዎች በ2002 ዓ.ም ላይ የነበረው የሰው ጫና ከ275.2 እስከ 171.65 ሰው/ካሬ ኪ.ሜ ይደርሳል።

በዚህ መረጃ መሰረት፣ በ2002 ዓ.ም ላይ በአቡነ ዮሴፍና ዝጊት ታሳቢ የማኅበረሰብ ጥብቅ ቦታ ዙሪያ ባሉ 8 ቀበሌዎች ይኖር የነበረው ሰው ብዛት 44,143 (22,013 ወንድና 22,130 ሴቶች) ነበር። ከዚህ ውስጥ፣ በሰሜን ወሎ ዞን ስር ባሉት የላስታ ላሊበላና ግዳን ወረዳ ነዋሪዎች ድርሻ እንደ ቅደም ተከተላቸው 53 እና 36 በመቶ ነው። ቀሪው 11 በመቶ በዋግ ኽምራ ብሄረሰብ አስተዳደር ዞን ስር ያለው የጋዝ ጊብላ ወረዳ አንድ ቀበሌ ድርሻ ነው። ይህ ታሳቢ የማህበረሰብ ጥብቅ ቦታ በሚያካልላቸው ቀበሌዎች በ2002 ዓ.ም ላይ የነበረው የሰው ጫና ከ192.7 እስከ 73 ሰው/ካሬ ኪ.ሜ ይደርሳል።

እንደ 2002 ዓ.ም የህዝብና ቤቶች ቆጠራ ውጤት፣ በአቦይ ጋራ ታሳቢ የማኅበረሰብ ጥብቅ ቦታ አካባቢ ከ47174 በላይ ሰዎች ይኖራሉ። በዚህ ታሳቢ የማህበረሰብ ጥብቅ ቦታ ዙሪያ ባሉ 7 የመኖሪያ ቀበሌዎች በ2002 ዓ.ም ላይ እንደነበረ የሚታሰበው የሰው ጫና ከ 210.7 እስከ 80.7 ሰው/ካሬ ኪ.ሜ ነው።

እንደ ሌሎች የኢትዮጵያ ከፍተኛ ቦታ አርሶ አደሮች በአቡነ ዮሴፍ፣ ዝጊትና አቦይ ጋራ ተራራዎች ታሳቢ ማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራ አካባቢዎች ለሚኖረው ጎብረተሰብ የሰብል እርሻና የቤት እንስሳት እርባታ ዋነኛ መተዳደሪያው ነው። በመሆኑም በአካባቢው የሚገኘው ውርጭና ውርጭ ቀመስ ስርዓተ ምህዳር ለእርሻ፣ ለቤት እንስሳት ግጦሽ፣ ለማገዶና ለኮንስትራክሽን

እንጨት ፍጆታ ወዘተ በማገልገል ለማህበረ ኢኮኖሚው በቀጥታና በተዘዋዋሪ ከፍተኛ ጠቀሜታዎችን ይሰጣል፡፡ በአካባቢው ገብስ፤ ድንች፣ ስንዴና ባቄላ አንደ ቅደም ተከተላቸው ተመራጭ ሆነው የሚመረቱ ሰብሎች ናቸው፡፡

ከሰብል አዝመራው ጎን ለጎን በጉና ተራራ ዙሪያ የሚኖረው የህብረተሰብ ክፍል የሚከውነው የቤት እንስሳት እርባታ፣ ለየቤተሰቡ የእርሻ ስራ፣ ለሰውና እቃ ማጓጓዣ፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ በመሄድ ላይ ካለው የስጋ ገበያ ገቢ ለማግኘት እያገለገለ ነው፡፡

በእነዚህ ምክንያቶች፣ የአካባቢው ነዋሪ የቀንድ ከብት፣ በግ፣ የጋማ ከብት፣ ዶሮና የንብ መንጋዎችን በልቅ ግጦሽ እያረባ ይኖራል፡፡ በመስክ ስራ ወቅት ለአንዳንድ ነዋሪዎች ከቀረበው መደበኛ ያልሆነ ቃለ መጠይቅ በተገኘው ምላሽ፣ በአካባቢው በመካከለኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ባለ አንድ ቤተሰብ በአማካኝ 2 በሬ፣ 1 ላም፣ 8 በግና ፍየል እና 2 የጋማ ከብት (ፈረስ፣ በቅሎና አህያ) ይኖረዋል፡፡ ከዚህ መረጃና ከየወረዳዎቹ የግብርና ጽ/ቤት በተገኘው መረጃ መሰረት፣ በአቡነ ዮሴፍ፣ ዝጊትና አቦይ ጋራ ተራራዎች ታሳቢ የማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራ ዙሪያ፣ ለሚገኘው ነዋሪ በግና ፍየል ማርባታ ቀዳሚ ምርጫ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

በመሆኑም፣ ከተፈጥሮ ሀብቱ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ ከጊዜ ወደ ጊዜ በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ በመሄድ ላይ ያለው ህዝብ ቁጥርና ሃብቱን የመጠቀም ፍላጎት ሀብቱን ጠብቆ ለማቆየት በሚደረጉ ጥረቶች መካከል ጉልህ የሆነ የአለመጣጣም ችግሮች አንዳሉ ከዚህ በፊት የተካሄደው የጥናት ውጤት ያረጋግጣል፡፡

6.2. በተፈጥሮ አካባቢው ላይ የሚታዩ ጫናዎች/ተጽዕኖዎች

በአቡነ ዮሴፍ፣ ዝጊትና አቦይ ጋራ ተራራዎች ታሳቢ የማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራዎች ዙሪያ የሚኖረው ህዝብና የቤት እንስሳት ቁጥርና ጫና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመምጣቱ ሳቢያ ለከፍተኛ የአፈር ክለት ተጋላጭ የሆኑት የውርጭና ውርጭ ቀመስ ስርዓተ ምህዳሮች በከፍተኛ ተጽእኖ ውሰጥ የሚገኙ ሲሆን በጥብቅ ስፍራው ከሚታዩት ዋና ዋና ችግሮች መካከልም፡-

- **ሰፊ የሆነ ልቅ ግጦሽ መኖር፡-** የአካባቢው ማኅበረሰብ ሙሉ በሙሉ በልቅ ግጦሽ እርባታ ሥርዓት የተቃኘ ልማድ ስላላቸው በጥናቱና ክለላው ወቅት እንደተረጋገጠው በጥብቅ ስፍራው ውስጥ የቤት እንስሳት የማይደርሱበት ቦታ የለም፡፡

- **የደን ጭፍጨፋ፡-** በአካባቢው ከልቅ ግጦሽ ጫና ጋር የደን ምንጣሮና ቃጠሎ በስፋት ስለሚከናወን ውጤቱም የአካባቢውን የውኃ ማማነት ከማስጠበቅ ይልቅ ከፍተኛ ቦረቦሮችን ፈጥሯል፡፡
- **ህገወጥ እርሻና የሰፈራ መስፋፋት፡-** ቅሪት የተፈጥሮ ሃብቱን በቅርበት ሆኖ ለመጠቀም በሚደረገው በሚደረገው እሽቅድምድም የመንደር ምስረታው እየተስፋፋ ከታች የሚኖረው ኀብረተሰብ ወደ ተራራው አናት በመውጣት በአሁኑ ስዓት ለሰው ልጅ መኖሪያ ተስማሚ ባልሆኑ ቦታዎች እስከ 3718 ሜትር ከባህር ወለል በላይ መንደሮች ይገኛሉ፡፡
- **የእርሻ መስፋፋት** ፡- በኢትዮጵያ በሚገኙ ከፍተኛ ቦታዎች በየዓመቱ ከ1.9 እስከ 3.5 ቢሊዮን ቶን የላይኛውና ለም የሆነው አፈር እንደሚታጠብ ጥናቶች የሚያሳዩ ሲሆን በዚህ ሳቢያም ወደ 10 ሚሊዮን የሚጠጉ አርሶ አደሮች የእርሻ መሬታቸው ከጥቅም ውጭ ይሆናል (EFAP, 1993; EHRS, 1984)፡፡ የዚህ አይነት ችግር ሰለባ የሆነው የአቡነ ዮሴፍ፣ ዝጊትና አቦይ ጋራ ተራራዎች ታሳቢ ማኀበረሰብ ጥብቅ ስፍራ ከፍተኛ የሆነ የእርሻ መሬት መስፋፋት በወረራ መልኩ እስከ 3800 ሜትር ከባህር ወለል በላይ ድረስ እየተካሄደበት ይገኛል፡፡
- **የወኃ ሃብት ብክነት/water resources degradation/፡-** የአቡነ ዮሴፍ፣ ዝጊትና አቦይ ጋራ ተራራዎች ታሳቢ ማኀበረሰብ ጥብቅ ስፍራ የተከዜ ተፋሰስ የውኃ ማማ በመሆኑ ለተፋሰሱ ገባር የሆኑ ድንበር ተሻጋሪ ወንዞች /የ20 ወንዞችና በርካታ ምንጮች/ መነሻ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ከላይ በተጠቀሱት እርስ በርሳቸው የተሰናሰሉ ችግሮች ድምር ውጤት ምክንያት በአካባቢው የሚዘንበው ዝናብ ወደ መሬት መስረግ ባለመቻሉ
    - በታችኛው የተፋሰስ ክልል ጎርፍን አባብሷል፣
    - የወንዞች ፍሰት ዓመቱን ሙሉ ከመሆን ይልቅ ወቅታዊ እንዲሆን አድርጓል፣
    - በታችኛው አካባቢ የውኃ አቅርቦት እጥረት በመፈጠሩ ምክንያት የመጠጥ ውኃ ችግር ተከስቷል፣
    - በታችኛው አካባቢ ደለል በዝቷል፣
    - የአየር መዛባትን ተከትሎ ድርቅን እያስፋፋ ነው፣
    - በተከዜ የኃይል ማመንጫ ግድብና በታችኛው ተፋሰስ አካባቢ የሚገኙ ወንዞች ለጎርፍና ደለል መሞላት መንስኤ ሆኗል፣

በመሆኑም የአቡነ ዮሴፍና አቦይ ጋራ አካባቢን መጠበቅ ለብዝሃ-ህይወት ጥበቃ ብቻ ሳይሆን የብዙ ወንዞች መነሻ በመሆኑ ይህን አካባቢ ከጉዳት መከላከል የአካባቢውን ነዋሪዎች ብቻ ሳይሆን የታችኛውን ተፋሰስ የውሃ ተጠቃሚ ለማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ ረጅም ጊዜ ሳይወስድ ህጋዊ ዕውቅና እንዲያገኝ ማስቻል ለነገ የማይባል ተግባር ነው፡፡

7. የማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራው የሚኖረው ጠቀሜታ

ሀ/ ሥነ-ምህዳራዊ ጠቀሜታ

- *ሰዎች ከተፈጥሮ ጋር ያላቸዉ ግብግብ ዘለቄታዊ የተፈጥሮ ገጽታ መኖርን ማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ እንዲሆን ማድረግ ያስችላል፡፡ በዚህም ዘለቄታዊ ጥቅም አለዉ*
- *በአካባቢው ያለው ስርዓተ ምህዳር እንዳይዛባ ከፍተኛ አስተዋፆ ያደርጋል ፡፡*
- *ለክለት ተጋላጭ የሆነው የከፍተኛ ቦታዎች ሰነምህዳር ለመጠበቅ ያስችላል፡፡*
- በማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው ውስጥ ያለው ብዝሃ ህይወት ሳይጠፋ እንዲኖር፡ያስችላል
- በአካባቢው የሚገኙ የዱር እንስሳትና ዕፅዋት በአይነትም ሆነ በብዛት ይጠበቃሉ፣
- የዱር እንስሳትና ዕፅዋት በቦታቸው እንዲጠበቁና እንዳይጠፉ ይረዳል፣
- የተስተካከለ የውሃ ሃብት እንዲኖር ያስችላል (ከማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራው የሚነሱ ምንጮችና ጂረቶች ዓመቱን በሙሉ እንዲፈሱ ያስችላል)፡፡

ለ/ ኢኮኖሚያው ጠቀሜታ

- በማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው ከጐብኝዎች ጋር ተያይዞ ከቱሪዝም አማራጭ ገቢዎች ለህብረተሰቡና ለመንግስት ገቢ ያስገኛል፣
- ከምርምርና ሣይንሳዊ ጥናት እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ የአካባቢውን ገቢና አቅም ያጐለብታል፣
- የኢኮ-ቱሪዝም እንቅስቃሴ ስለሚስፋፋ ለአካባቢው ህብረተሰብ አንድ የገቢ ምንጭ ይሆናል፡፡
- የአካባቢው የአየር ሚዛን ስለሚጠበቅ ከእርሻ ስራ የሚገኘው ገቢ ዘላቂና አስተማማኝ ይሆናል፡፡
- በሆቴልና አገልግሎት በመስጠት በርካታ ነዋሪዎች ኑሯቸዉን ማሻሻል ይችላሉ ተጨማሪ እዉቀትም ይኖራቸዋል፡፡

ሐ/ ማህበራዊ ጠቀሜታ

- ዓለማቀፋዊና ማህበረሰባዊ የሆኑ ጠቃሚ የባህልና ልምድ ልውውጥ ይኖራል፣
- በአካባቢው የሚገኙ ነዋሪዎች የተፈጥሮ ቦታውን ለመጠበቅም ሆነ በአገባቡ ለመጠቀም የሚያስችል ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል። ዘላቂ የሆነ የጎሳ አጠቃቀም እንዲኖር ያስችላል።

መ/ ሳይንሳዊ ጠቀሜታ

- የዱር እንስሳትና ዕፅዋትን ባሉበት ሁኔታና በተፈጥሮአዊ አኗኗራቸው ለሚደረግ ምርምር በማእከልነት ያገለግላል።
- የባህላዊ መድሃኒቶችን ደህንነት በመጠበቅና በመንከባከብ ጥቅም ላይ በማዋል ሣይንሳዊ ጥናትንም ለማካሄድ ይረዳል።
- በመጥፋት ላይ ላሉ የዱር እንስሳትና እጽዋት ሳይንሳዊ ምርምር ሊድረግ ያስችላል።
- በጎሳውና ገጽታው ለከባቢያዊ ደህንነት፤ ለብዝሃ ህይወትና ለስርዓተ ምህዳር መስተካከል ያላቸው አስተዋጽዖ ይታወቃል በዚህ ረገድ ለሚደረጉ ምርምሮች የመስክ ላቦራቶር ሊሆን ይችላል።

መ/ የተፈጥሯዊነት ጠቀሜታ

- ተፈጥሯዊነትን ጠብቆ ለመቆየት ያስችላል። በውስጡ ያሉትን ብዝሃ ህይወትና ሌሎች (አፈር፤ዉሃና የመሬት አቀማማጥ) በተፈጥሮአዊ ገጽታቸው ቆይተው ዘለቂታ ባለው መልክ ጥቅም እነዲሰጡና ተፈጥሮአዊ ይዘታቸው እንዳይጓደል ይረዳል።

ሠ/ የመስህብነት ጠቀሜታ

- አካባቢው የሰው ልጅን ቀልብ ሊገዙ የሚችሉ ማራኪ ገጽታዎችን የያዘ ከመሆኑም በተጨማሪ ቀይ ቀበሮን እንደልብ ሊያዩበት የሚችል በመሆኑና በብዙ ተፈጥሯዊና ባህላዊ ቅርሶች ተከበበ ስለሆነ የመስህብነት ጠቀሜታውን የጎላ ያደርገዋል።

ስለሆነም ይህ የበርካታ ብዝሐ ህይወት መጠለያና የምስራቅ አፍሪካ የውኃ ማማ የሆነ አካባቢ በማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራ አጠባበቅ ሥርዓት መሰረት ዘላቂ በሆነ ጥበቃና አጠቃቀም ተጠብቆ

ለትውልድ እንዲተላለፍ በጥብቅ ስፍራነት ተከልሎ የሚያበረክተው አኮኖሚያዊ፣ ስነምህዳራዊ፣ ሳይንሳዊና ማኅበራዊ ጠቀሜታውና ዓለማቀፋዊ አስተዋጸው ከፍ ማለት እንዳለበት ያሳያል፡፡

8. የማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራው የወደፊት የጥበቃ ሁኔታ

የአቡነ ዮሴፍ፣ ዝጊትና አቦይ ጋራ ተራራዎች ታሳቢ የማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራ አስከአሁን ድረስ ምንም አይነት ጥበቃ ስለማይደረግለት በእልቂት ስጋት ላይ ያለ አካባቢ ስለሆነ ለወደፊት አስተዳደሩን በተመለከተ ተጠሪነቱ ለክልሉ ባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮና ለአቡነ ዮሴፍና አቦይ ጋራ ልማትና ጥበቃ ም/ቤቶች የሆነ ጽ/ቤት ማቋቋም ያስፈልጋል፡፡ የጥበቃ ስራውም በመንግስት በሚቀጠሩ የመንግስት ስካውቶችና በማኅበረሰቡ በሚመረጡ የማኅበረሰብ ስካውቶች የጥበቃ ስራው ይካሄዳል፡፡ የጥብቅ ስፍራውን ከአካባቢው ማኅበረሰብ ጋር በመሆን ለማልማትና ለመጠበቅ የሚቋቋመው ተቋም ለስራው አመች በሆነ ቦታ ይቋቋማል፡፡ የሚቋቋመው ጽ/ቤትም በማህበረሰብ ጥብቅ የስፍራው ውስጥ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡-

- የማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራውን የሚጠብቁ የአካባቢ የደን ጥበቃ ስፍራዎችን መቆጣጠር፣
- ከጎብኝዎች ሚሰበሰብ ገንዘብን ለአካባቢው ጎብረተሰብ ልማት በአግባቡ ሚውልበትን ሁኔታ ይከታተላል፣
- የጓሳውን መዝጊያና መክፈቻ ጊዜ የቆጣጠራል ያስከብራል (ለሁለት ዓመት ከአስር ወራት ከተዘጋ በኋላ ለሁለት ወራት ክፍት ይሆናል)፣
- ከቤትእንስሳት ወደ ዱር እንስሳት የሚተላለፉ የእንስሳት በሽታዎች ላይ ቁጥጥር ያደርጋል፣
- የማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራውን በተመለከተ የአካባቢውን ማኅበረሰብ በማስተባበር የልማት ስራዎችን ያከናውናል፣
- በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ውስጥ የዱር እንስሳት ቁጥጥርና ጥበቃ እንዲካሄድ ያደርጋል፣

9. ማጠቃለያ

በከፍተኛ ተጽእኖ ውስጥ የሚገኘውና ምንም ዓይነት የአጠቃቀምና አጠባበቅ ስርዓት የሌለውን የአቡነ ዮሴፍ፣ዝጊትና አቦይ ጋራ ተራራዎች የማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራና አካባቢውን ከጥፋት ለመታደግ እንዲሁም የአካባቢውን ማኅበረሰብ በዘላቂነት ተጠቃሚ ለማድረግ እንዲቻል ቢሮው ከፍራንክፈርት ዞሎጂካል ሶሳይቲ ጋር በመቀናጀት በ2005 ዓ.ም፡-

- በአቡነ ዮሴፍና አቦይ ጋራ የተራራ ሰንሰለቶችና አካባቢው የማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም መሰረታዊ የብዝሐ ህይወትና ማኅበረ ኢኮኖሚ የዳሰሳ ጥናት ተካሂዷል፣
- የአካባቢው ህዝብና አስተዳደር፣ ፍራንክፈርት ዚኦሎጂካል ሶሳይቲ ከተባለ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ጋር በመተባበር ቅሪት ሀብቱ በአካባቢው ማኅበረሰብ ተጠብቆና ለምቶ ለቱሪዝም ገበያ የሚቀርቡበትን ተግባራት አከናውነዋል። እስካሁን ባደረጉት ጥረትም፣ የተፈጥሮ ቦታዎቹ ድንበር ተከልሎ በመጠበቅ ላይ ይገኛል። በተለይ ለአቡነ ዮሴፍ ማኅበረሰብ ጥብቅ ቦታነት በተከለለው አካባቢ የሚኖረው ህዝብ፣ የተፈጥሮ ሃብቱን በመጠበቅና በማልማት በአግባቡ ለመጠቀም የሚያስችላቸውን መተዳደሪያ ደንብ በስምምነት አጽድቋል። በደንቡ መሰረት፣ የአካባቢው ነዋሪ መርጦ ባደራጃቸው ወኪሎቹ በኩል የተፈጥሮ ቦታውን ለሚጎበኙ የሀገር ውስጥና ዓለም አቀፍ ጎብኚዎች አገልግሎት በማቅረብ ተጠቃሚ በመሆን ላይ ይገኛል።
- በክለላው ወቅትም ወደ 178 የሚደርሱ ከአመራር፣ ከባለሙያዎችና ከአካባቢው ሽማግሌዎች የተውጣጣ ኃይል በስራው ሙሉ ተሳታፊዎች ነበሩ። በአጠቃላይ የታሳቢ ማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራውና የቀበሌዎች ወሰን ምልክቶችን የመለየትና 733 የጂፒኤስ ንባቦችን (ከወሰን መለያ ቁጥር 001 እስከ 527 ለአቡነ ዮሴፍ ማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራ እና ከወሰን መለያ ቁጥር 001 እስከ 206 ደግሞ ለአቦይ ጋራ ማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራ) በመውሰድ የተከለለ ሲሆን ከየቀበሌው በተመረጡ የዳር ድንበር ክለላ የኮሚቴ አባላት ስምምነት የተረጋገጠውን ቃለ ጉባኤ ሁሉም ቀበሌዎች ጉዳዩን አምነውበት ስምምነቱን አጽድቀውታል። የሁሉም አዋሳኝ ቀበሌዎች የዳር ድንበር ወሰን ክለላ ከተጠናቀቀ በኋላ በቀበሌ ደረጃ የጸደቀውን መነሻ በማድረግ የተያዘው ቃለ ጉባኤና የኮሚቴዎችን የስምምነት ፊርማ የወረዳው ካቢኔ ተወያይቶ ከመረመረ በኋላ በወረዳ ደረጃ እንዲጸድቅ ተደርጓል። በቀበሌና በወረዳ ደረጃ የጸደቀው የዳር ድንበር ወሰን የክለላ ሰነድ አንድ ኮፒ ለየቀበሌው አስተዳደር፣ አንድ ኮፒ ለየወረዳው አስተዳደር፣ አንድ ኮፒ ለየወረዳው አካባቢ ጥ/መ/አ/አ/ ጽ/ቤት፣ ዋናው ኮፒ ደግሞ ለክልሉ ባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ እንዲደርስ ተደርጓል።
- ከጥናትና ክለላ ሪፖርቶች በመነሳት ረቂቅ ደንብ ተዘጋጅቶ ከ80 በላይ የባለድርሻ አካላትና የማኅበረሰቡ ተወካዮች በተገኙበት አውደ ጥናት በላል ይበላና ሙጃ ከተማዎች ላይ በማካሄድ በውይይት ወቅት የተሰጡ አስተያየቶችን በማካተት ረቂቅ ደንቡን ለማበልጸግ ጥረት ተደርጓል፣

- እነዚህ ጅምር ጥረቶች ግን በአግባቡ የተደራጁና የተጠናከሩ አይደሉም፡፡ ለዚህ ደግሞ፣ የተፈጥሮ ቦታዎቹ ድንበር በመለየት እና አካባቢዎቹን አልምቶ ለመጠቀም በማኅበረሰቡ የፀደቀው ደንብ በሚመለከተው የህግ አውጪ አካል ተገቢው የህግ እውቅናና ከለላ አለማግኘታቸው በግንባር ቀደም ተጠቃሽ ምክንያት ነው፡፡ የባህል ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ (የባ/ቱ/ፓ/ል/ቢሮ) በአዋጅ ከክልሉ ህዝብና መንግስት በተሰጠው ስልጣን መሰረት፣ ይህ ክፍተት የሚሸፈንበትን ምቹ ሁኔታ የመፍጠር ኃላፊነት አለበት፡፡ በመሆኑም፣ የቢሮው የዱር እንስሳት ጥናት፣ ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ስራ ሒደት ይህን ኃላፊነት ለመወጣት ባዘጋጀው የ5 አመት የልማትና እድገት እቅድ ላይ፣ የማኅበረሰብ ጥብቅ ቦታዎቹን በማቋቋም የተፈጥሮ ሃብቱን ለማልማትና በአግባቡ ለመጠቀም በአካባቢው የተጀመሩ ጥረቶች የህግ እውቅና አግኝተው ይበልጥ እንዲጠናከሩ የማድረግ ስራ ትኩረት ከሰጣቸው ስራዎቹ መካከል ግንባር ቀደም ተጠቃሽ ነው፡፡
- የዚህ ሰነድ ዓላማም፣ ለታሳቢ የማኅበረሰብ ጥብቅ ቦታዎቹ እውቅና ለሚሰጠው የህግ አውጪ አካል ለሚቀርበው ደንብ ደጋፊ ሰነድ መነሻ የሚሆኑ መረጃዎችን አሰባስቦ ለማደራጀት ነው፡፡

በአጠቃላይ የአቡነ ዮሴፍ፣ ዝጊትና አቦይ ጋራ ተራራዎች ታሳቢ ማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራ ጥብቅ ቦታ የመሆን አቅም ባለው የተፈጥሮ አቀማማጥ፤ ብዝሐ ህይወትና የሚሠጠው ጠቀሜታ የተገለጸ ቢሆንም በጥናቱ እንደተረጋገጠው ወሳኙ ያሉትን ችግሮች በመቅረፍና የተፈጥሮ ሃብቱ ወደ ነበረበት የመመለስ ጥረት ላይ የወደቀ ነው፡፡ ለዚህም ሁሉም አጋር አካላት የየድርሻቸውን መወጣት ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ ከሆነ የአቡነ ዮሴፍ፣ ዝጊትና አቦይ ጋራ ተራራዎች ታሳቢ ማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራ በመሆን የሚከተሉትን ዓላማዎች የሚያሳካ ይሆናል፡፡

- ***ለብዝሃ ህይወት ጥበቃ፡*** ባለው ስርዓተ-ምህዳር ውስጥ የብዝሐ ህይወት ሃብትን የዘቦታ/Insitu conservation/ ልማትና ጥበቃ ለማካሄድ የሚያስችል የዕጽዋትና እንሰሳት ስብጥርን በማጥናት፤በማልማትና በመጠበቅ ለተተኪ ትውልደ ለማሰተላላፍ፡፡
- ***ማራኪ የመሬት አቀማመጥንና ተፈጥሮአዊ ገፅታን ለመጠቀምና ለማቆየት፡***-ተፈጥሮአዊና ማራኪ የሆነውን የመሬት አቀማመጥ ለሰው ልጆች አዕምሮ ማደሻ በማድረግ የመዝናኛ እድሎችን መፍጠርና በተፈጠሮአዊ ገፅታው በማቆየት በዚህ ሁኔታ በውስጡ ያሉትን ተፈጥሮአዊ ሃብቶች በዘላቂ ቱሪዝምና በተመጣጣኝ አጠቃቀም ጥቅም ላይ ለማዋል፡፡

- ***ለትምህርትና ምርምር፡*** ብዝሃ ሕይወትንና ተፈጥሮአዊ አካባቢዎችን የትምህርትና የምርምር ማዕከል በማድረግ በዘርፉ የሚጠበቀውን ሳይንሳዊ እድገት ለማመጣትና አግባብ ባለው መንገድ ለማልማትና ለመጠቀም፡፡
- ***በዘላቂ ቱሪዝም ኢኮኖሚያዊ ልማት ለማስፋፋት፡*** የተፈጥሮ መዝናናዎችን በማስፋፋትና በኢኮቱሪዝም በመደራጀት ለጎብኝዎች በሚሠጥ አገልግሎት የነዋሪውን ህዝብ ኑሮ ማሻሻልና መሰረተ ልማቶችን ለማሳደግ፤ በዚህም ዋነኛ የገቢ ምንጭ በመሆን በኢኮኖሚው እድገት ከፍተኛ አስተዋጾ ለማበርከት ያስችላል፡፡
- ***አካባቢው የሚሰጠውን አገልግሎት /Ecosystem services/ በተሸለ ሁኔታ ጥቅም ላይ እንዲውል ለማስቻል፡*** የአቡነ ዮሴፍና አቦይ ጋራ አካባቢ በክልሉ ለሚገኘው የተከዜ አብይ ተፋሰስ ገባር የሆኑ ከ20 በላይ ዋና ዋና ወንዞች እና በርካታ ምንጮች መነሻ በመሆኑ በተፋሰሱ የላይኛው አካልና በታችኛው አካባቢ የሚኖሩ ለመጠጥና ሌሎች አገልግሎቶች ሊውል የሚችል ውኃ ማግኘት የሚያስችል ቦታ ከመሆኑም በተጨማሪ የተከዜ ግድብ ህልውናም የሚመሰረተው በአቡነ ዮሴፍ፣ አቦይ ጋራና መሰል ስርዓተ ምህዳር ባላቸው አካባቢዎች በመሆኑ ይህን አካባቢ ማልማትና መጠበቅ የተከዜን ግድብ ደህንነት መጠበቅ ነው፡፡ ሰለዚህ የአቡነ ዮሴፍና አቦይ ጋራን ስርዓተ ምህዳር መጠበቅ የአካባቢውን የአየር ሚዛን ለመጠበቅ ያስችላል፡፡

ዕዝል1- የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው ወሰን ዝርዝር መግለጫ

የማህበረሰብ ጥብቅ ቦታን አከላለልና አዋሳኝ ሥፍራዎችን በኬክሮስ/ላቲቲዩድ/ እና በኬንትሮስ /ሎንግቲዩድ/ ነጥቦች የሚያሳዬው ዝርዝር መግለጫ ከዚህ በታች ተመልክቷል፡፡

- **የአቡነ ዮሴፍና ዝጊት ተራራ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራ**

10.1.1 የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራውን በሰሜን አቅጣጫ ከሚያዋስኑት የላስታና ግዳን ወረዳ ቀበሌዎች የእንጃፋትና አጢማጣ ቀበሌ ድንበር ማንጥር ወንዝ ላይ 12 ዲግሪ 14 ደቂቃ 20.20 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 07 ደቂቃ 31.55 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አንድን መነሻ በማድርግ፣

10.1.2 ከዚያም የእንጃፍትን (017) ቀበሌ ድንበር በመከተል በምዕራብ አቅጠጫ ዝንጆሮ መጠበቂያው ላይ 12 ዲግሪ 07 ደቂቃ 55.40 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 13 ደቂቃ 55.43 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሁለት፣

10.1.3 ከዚያም ወደ ደቡብ አቅጣጫ በመታጠፍ ምረጉ ድንጋይ ጎጥ ላይ 12 ዲግሪ 07 ደቂቃ 29.27 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 13 ደቂቃ 32.77 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሶስት፣

10.1.4 ከዚያም ወደ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ ጎጆ መስሪያና ነጭቱ መስክን በማለፍ ጥልቁ ሜዳ ላይ 12 ዲግሪ 07 ደቂቃ 53.52 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 13 ደቂቃ 09.10 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አራት፣

10.1.5 ከዚያም ወደ ሰሜን አቅጣጫ በመታጠፍ ወይኒቱ ውኃና ገላው በረትን በማለፍ እጅጉ ጅብራ ላይ 12 ዲግሪ 08 ደቂቃ 15.54 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 13 ደቂቃ 24.01 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አምስት፣

10.1.6 ከዚያም በተመሳሳይ አቅጣጫ በመከተል እንጃፋትና አቡነ ዮሴፍ (016) ቀበሌ ድንበር ቁሲት ተራራ ላይ 12 ዲግሪ 08 ደቂቃ 57.82 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 13 ደቂቃ 39.76 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ስድስት፣

10.1.7 ከዚያም የአቡነ ዮሴፍ ቀበሌ ድንበር በመከተል ወደ ደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ በመሄድ ጨው ማራገፊያ ጎጥ ላይ 12 ዲግሪ 08 ደቂቃ 47.42 ሴኮንድ ሰሜን እና በ39 ዲግሪ 13 ደቂቃ 26.7 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሰባት፣

10.1.8 ከዚያም ወደ ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ ደንሳና ድባና ገብረ ህይወት ጎጥን በማለፍ ጎጆው ጎጥ ላይ 12 ዲግሪ 08 ደቂቃ 42.72 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 12 ደቂቃ 52.27 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ስምንት፣

10.1.9 ከዚያም ወደ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ ሌባ ኩፍ ጎጥን በማለፍ ጋጎ መከመርያ ጎጥ ላይ 12 ዲግሪ 09 ደቂቃ 00.61 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 12 ደቂቃ 35.51 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ዘጠኝ፣

10.1.10 ከዚያም ወደ ደቡብ አቅጣጫ በመታጠፍ ጥርጥሩ ላይ 12 ዲግሪ 08 ደቂቃ 29.40 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 12 ደቂቃ 19.07 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አስር፣

10.1.11 ከዚያም ወደ ተመሳሳይ አቅጣጫ በመከተል አቲፍ አርንቋ ጎጥን በማለፍ ኮይሎ ድንጋይ ላይ 12 ዲግሪ 08 ደቂቃ 12.67 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 12 ደቂቃ 08.93 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አስራ አንድ፣

10.1.12 ከዚያም ወደ ምዕራብ አቅጣጫ በመሄድ ዝቢት ላይ 12 ዲግሪ 08 ደቂቃ 12.53 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 11 ደቂቃ 39.06 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አስራ ሁለት፣

10.1.13 ከዚያም ወደ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ ዝቢት ጎጥ ላይ 12 ዲግሪ 08 ደቂቃ 26.93 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 11 ደቂቃ 24.77 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አስራ ሶስት፣

10.1.14 ከዚያም ወደ ሰሜን አቅጣጫ በመከተል እንጆራ መጋገርያው ጎጥን በማለፍ ጅብራው ላይ 12 ዲግሪ 09 ደቂቃ 21.55 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 11 ደቂቃ 30.54 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አስራ አራት፣

10.1.15 ከዚያም ወደ ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ ብርግዱ ገደል ጎጥን በማለፍ ዶሽ ወደቅ ላይ 12 ዲግሪ 09 ደቂቃ 45.12 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 10 ደቂቃ 41.05 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አስራ አምስት፣

10.1.16 ከዚያም ወደ ደቡብ አቅጣጫ በመታጠፍ ነጩ ድንጋይ ጎጥን በማለፍ ሞላላው ድንጋይ ላይ 12 ዲግሪ 09 ደቂቃ 18 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 10 ደቂቃ 27.60 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አስራ ስድስት፣

10.1.17 ከዚያም ወደ ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ ንጉሱ ዋሻን በማለፍ ወይፈን ማቅኛው ጎጥ ላይ 12 ዲግሪ 09 ደቂቃ 41.54 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 09 ደቂቃ 49.33 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አስራ ሰባት፣

10.1.18 ከዚያም በተመሳሳይ አቅጣጫ በመከተል አምጃው ጎጥ ላይ 12 ዲግሪ 09 ደቂቃ 48.53 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 09 ደቂቃ 18.33 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አስራ ሰምንት፣

10.1.19 ከዚያም ወደ ሰሜን አቅጣጫ በመታጠፍ የላስታና የጋዝጊብላ ወረዳ ቀበሌዎች የአቡነ ዮሴፍ እና ሐዋርያው ጴጥሮስ ቀበሌ ድንብር ላይ 12 ዲግሪ 10 ደቂቃ 06.00 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 09 ደቂቃ 27.80 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አስራ ዘጠኝ፣

10.1.20 ከዚያም ወደ ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ የሐዋርውያ ጴጥሮስ ቀበሌ ድንበርን በመከተል ከፋቲ ላይ 12 ዲግሪ 10 ደቂቃ 22.90 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 08 ደቂቃ 36.52 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሀያ፣

10.1.21 ከዚያም ወደ ደቡብ አቅጣጫ በመታጠፍ አቂቦ ላይ 12 ዲግሪ 08 ደቂቃ 46 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 08 ደቂቃ 14.9 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሀያ አንድ፣

10.1.22 ከዚያም ወደ ተመሳሳይ አቅጣጫ በመከተል የሐዋርውያ ጴጥሮስና ወደብየ (015) ቀበሌ ድንበር ላይ 12 ዲግሪ 07 ደቂቃ 50.25 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 08 ደቂቃ 24.83 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሀያ ሁለት፣

10.1.23 ከዚያም ወደ ሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ በግ ማጠቢያው ጎጥ ላይ 12 ዲግሪ 08 ደቂቃ 45.40 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 09 ደቂቃ 24.48 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሀያ ሶስት፣

10.1.24 ከዚያም ወደ ደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ ጀሞ ገደል እና ነጩ ቁትን በማለፍ ላጣው ጎጥ ላይ 12 ዲግሪ 07 ደቂቃ 31.41 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 10 ደቂቃ 09.23 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሀያ አራት፣

10.1.25 ከዚያም ወደ ደቡብ አቅጣጫ በመታጠፍ የወደብየና የጠልፈጢት ቀበሌ ድንበር ጋንዳፉ ዋሻ ላይ 12 ዲግሪ 06 ደቂቃ 39.92 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 09 ደቂቃ 42.73 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሀያ አምስት፣

10.1.26 ከዚያም ወደ ሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ ደመና ዋሻን በማለፍ ጥቁር ዋሻ ላይ 12 ዲግሪ 07 ደቂቃ 13.80 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 10 ደቂቃ 47.80 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሀያ ስድስት፣

10.1.27 ከዚያም ወደ ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ ዝንጀሮ አልጋ ጎጥ ላይ 12 ዲግሪ 06 ደቂቃ 43.15 ሴኮንድ ምስራቅ እና 39 ዲግሪ 11 ደቂቃ 15.70 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሀያ ሰባት፣

10.1.28 ከዚያም በተመሳሳይ አቅጣጫ በመንገዝ አቶ ወንዴ እርሻ ደንበር ላይ 12 ዲግሪ 06 ደቂቃ 44.29 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 11 ደቂቃ 54.15 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሀያ ስምንት፣

10.1.29 ከዚያም ወደ ደቡብ አቅጣጫ በመታጠፍ የላስታና ግዳን ወረዳ ቀበሌዎች የጠልፈጢትና የቀይ ገደል ቀበሌ ድንበር አምጃው ባህር ላይ 12 ዲግሪ 05 ደቂቃ 01.58 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 11 ደቂቃ 57.64 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሀያ ዘጠኝ፣

10.1.30 ከዚያም ወደ ሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ ጭማ መቀጥቀጫውን በማለፍ መሳዩ ድንጋይ ላይ 12 ዲግሪ 05 ደቂቃ 28.60 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 12 ደቂቃ 36.76 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሰላሣ፣

10.1.31 ከዚያም ወደ ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ ወደሉ ተራራን በማለፍ ወንዙ ላይ 12 ዲግሪ 06 ደቂቃ 01.25 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 14 ደቂቃ 04.26 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሰላሣ አንድ፣

10.1.32 ከዚያም ወደ ደቡብ አቅጣጫ በመታጠፍ የቀይ ገደልና መስቀለሳስ ቀበሌዎች ድንበር አርጎ ዋሻ ላይ 12 ዲግሪ 04 ደቂቃ 49.19 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 14 ደቂቃ 25.53 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሰላሣ ሁለት፣

10.1.33 ከዚያም ወደ ሰሜን አቅጣጫ በመታጠፍ አፋፉን በማለፍ ገደሉ ስር 12 ዲግሪ 05 ደቂቃ 58.05 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 14 ደቂቃ 54.24 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሰላሣ ሶስት፣

10.1.34 ከዚያም ወደ ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ ነብሩ ሰፈርን በማለፍ ተስፋ ካምፕ ላይ 12 ዲግሪ 06 ደቂቃ 15.40 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 16 ደቂቃ 04.63 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሰለሣ አራት፣

10.1.35 ከዚያም ወደ ሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ የመስቀለሳስና የአጢማጣ ቀበሌዎች ድንበር ይባር ላይ 12 ዲግሪ 06 ደቂቃ 45.28 ሴኮንድ ምስራቅ እና 39 ዲግሪ 16 ዲቂቃ 45.55 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሰላሣ አምስት፣

10.1.36 ከዚያም ወደ ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ ሰማቱ ተራራ ላይ 12 ዲግሪ 07 ደቂቃ 09.15 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 16 ደቂቃ 04.61 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሰላሣ ስድሰት፣

10.1.37 ከዚያም ወደ ደቡብ አቅጣጫ በመታጠፍ ቁንዶ ጭማ ላይ 12 ዲግሪ 06 ዲግሪ 45.26 ደቂቃ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 15 ደቂቃ 58.57 ሴኮንድ ምሰራቅ ጉልት ቁጥር ሰላሣ ሰባት፣

10.1.38 ከዚያም ወደ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ መፍለቂያው ወኃ ላይ 12 ዲግሪ 07 ደቂቃ 22.07 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 15 ደቂቃ 03.09 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሰላሣ ስምንት በመሆን ከጉልት ቁጥር አንድ ጋር ዙሮ ይገጥማል።

- **የአቦይ ጋራ ተራራ የማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራ**

10.1.39 የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራውን በሰሜን አቅጣጫ ከሚያዋስነው ወፍጫት (030) ቀበሌ ካሳው እርሻ ላይ 12 ዲግሪ 05 ደቂቃ 55.84 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 21 ደቂቃ 16.21 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አንድን መነሻ በማድርግ፣

10.1.40 ከዚያም ወደ ሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ ነብሩ ጉሬ ትልቁ አለት ላይ 12 ዲግሪ 06 ደቂቃ 07.62 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 21 ደቂቃ 25.22 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሁለት፣

10.1.41 ከዚያም ወደ ምስራቅ አቅጣጫ በመታጣፍ ከቆቦ ላሊበላ በሚወስደው መንገድ ብዙ ድንጋይ ላይ 12 ደቂቃ 05 ደቂቃ 46.66 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 22 ደቂቃ 09.16 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሶስት፣

10.1.42 ከዚያም ወደ ሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ ጅብራ ወንዝ ላይ 12 ዲግሪ 05 ደቂቃ 51.10 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 22 ዲቂቃ 27.82 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አራት፣

10.1.43 ከዚያም ወደ ሰሜን አቅጣጫ በመከተል ወፍጫት እና አሹኳና ቀበሌ ድንበር ሽማኒ ሁዳዲ ላይ 12 ዲግሪ 06 ደቂቃ 16.95 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 22 ደቂቃ 47.81 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አምስት፣

10.1.44 ከዚያም ወደ ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ የአሹኳና እና ቱባ ቀበሌ ድንበር ፍሪዳ ማርጃ ላይ 12 ዲግሪ 06 ደቂቃ 08.15 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 23 ደቂቃ 16.34 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ስድስት፣

10.1.45 ከዚያም ወደ ደቡብ አቅጣጫ በመታጠፍ ሽለቆውን በማለፍ ምንጩ ላይ 12 ዲግሪ 05 ደቂቃ 32.32 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 22 ደቂቃ 46.95 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሰባት፣

10.1.46 ከዚያም ወደ ደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ ፊርሱ ሳር ላይ 12 ዲግሪ 05 ደቂቃ 05.89 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 23 ደቂቃ 03.52 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሰምንት፣

10.1.47 ከዚያም ወደ ሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ ዞርአምባ ጎጆ ላይ 12 ዲግሪ 05 ደቂቃ 21 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 23 ደቂቃ 35.73 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ዘጠኝ፣

10.1.48 ከዚያም ወደ ደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ አምባ በርን በማለፍ መንታው መንገድ ላይ 12 ዲግሪ 04 ደቂቃ 38.37 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 23 ደቂቃ 35.86 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አስር፣

10.1.49 ከዚያም ወደ ሰሜን አቅጣጫ በመታጠፍ ግድብ ተራራን በማለፍ አደራ ሸንጎ ላይ 12 ዲግሪ 05 ደቂቃ 03.60 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 24 ደቂቃ 00.41 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አስራ አንድ፣

10.1.50 ከዚያም ወደ ደቡብ አቅጣጫ በመታጠፍ ግድብ መድኃኒዓለም ላይ 12 ዲግሪ 04 ደቂቃ 44.41 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 24 ደቂቃ 06.37 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አስራ ሁለት፣

10.1.51 ከዚያም ወደ ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ የቱባ እና የበቅሎ ማነቂያ ቀበሌ ድንበር ሰሳው መጥበሻ ላይ 12 ዲግሪ 04 ደቂቃ 33.63 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 23 ደቂቃ 26.96 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አስራ ሶስት፣

10.1.52 ከዚያም ወደ ደቡብ አቅጣጫ በመታጠፍ ጭንጫው አውድማ ላይ 12 ዲግሪ 03 ደቂቃ 27.46 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 23 ደቂቃ 42.44 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አስራ አራት፣

10.1.53 ከዚያም ወደ ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ ቀጭኑ ገደል ከህገ ወጥ እርሻው ጥግ 12 ዲግሪ 03 ደቂቃ 12.65 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 23 ደቂቃ 14.44 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አስራ አምስት፣

10.1.54 ከዚያም ወደ ደቡብ አቅጣጫ በመታጠፍ አማኑኤል ጠበል ላይ 12 ዲግሪ 01 ደቂቃ 56.47 ሴኮንደ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 23 ደቂቃ 39.50 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አስራ ስድስት፣

10.1.55 ከዚያም ወደ ተመሳሳይ አቅጣጫ በመከተል ንጉስ አርብ ላይ 12 ዲግሪ 00 ደቂቃ 43.86 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 24 ደቂቃ 30.19 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አስራ ሰባት፣

10.1.56 ከዚያም ወደ ተመሳሳይ አቅጣጫ በመከተል ትንሽቱ ገደል ላይ 11 ዲግሪ 59 ደቂቃ 30.85 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 24 ደቂቃ 45.75 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አስራ ስምንት፣

10.1.57 ከዚያም ወደ ሰሜን አቅጣጫ በመታጠፍ ፉጉ ላይ 12 ዲግሪ 00 ደቂቃ 39.40 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 23 ደቂቃ 48.68 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት አስራ ዘጠኝ፣

10.1.58 ከዚያም ወደ ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ አገውጅል ደጋ የወል መሬት ላይ 12 ዲግሪ 59 ደቂቃ 21.84 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 22 ደቂቃ 40.81 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሀያ፣

10.1.59 ከዚያም ወደ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ የበቅሎ ማነቂያ እና የጌስታ (014) ቀበሌ ድንበር ሰለሽስት ላይ 12 ዲግሪ 00 ደቂቃ 17.86 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 22 ደቂቃ 00.31 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሀያ አንድ፣

10.1.60 ከዚያም ወደ ሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ ጠለፈጢት ቀበሌ ውስጥ ቆሎ ምድር አስቱ ላይ 12 ዲግሪ 01 ደቂቃ 18.49 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 23 ደቂቃ 02.73 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሀያ ሁለት፣

10.1.61 ከዚያም ወደ ሰሜን አቅጣጫ በመታጠፍ ግድግዳ ማረፊያ የወል መሬት ላይ 12 ዲግሪ 01 ደቂቃ 59.87 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 23 ደቂቃ 05.87 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሀያ ሶስት፣

10.1.62 ከዚያም ወደ ሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ አሁንም ከዚያው ግድግዳ ማረፊያ ላይ 12 ዲግሪ 02 ደቂቃ 16.04 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 22 ደቂቃ 50.05 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሀያ አራት፣

10.1.63 ከዚያም ወደ ሰሜን አቅጣጫ በመታጠፍ መንገዱን በማለፍ ክራንክሩ ላይ 12 ዲግሪ 03 ደቂቃ 27.30 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 22 ደቂቃ 50.11 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሀያ አምስት፣


10.1.64 ከዚያም ወደ ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ ቀበሮ ሜዳ መንገዱ ላይ 12 ዲግሪ 02 ደቂቃ 22.93 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 22 ደቂቃ 30.58 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሀያ ስድስት፣

10.1.65 ከዚያም ወደ ሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ የጌስታ እና የደንገልሳ ቀበሌ ድንበር ብልጭቱ ላይ 12 ዲግሪ 04 ደቂቃ 24.64 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 21 ደቂቃ 29.09 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሀያ ሰባት፣


10.1.66 ከዚያም በተመሳሳይ አቅጣጫ በመጓዝ ቁሚቱ ድንጋይ/ መንገዱ/ ላይ 12 ዲግሪ 04 ደቂቃ 56.11 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 21 ደቂቃ 39.61 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሀያ ስምንት፣

10.1.67 ከዚያም ወደ ተመሳሳይ አቅጣጫ በመከተል የወርቅ አውጡ እና የወፍጫት ቀበሌ ድንበር ገና መጫወቻው ላይ 12 ዲግሪ 05 ደቂቃ 41 ሴኮንድ ሰሜን እና 39 ዲግሪ 22 ደቂቃ 06.87 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሀያ ዘጠኝ በመሆን ከጉልት ቁጥር አንድ ጋር ዙሮ ይገጥማል።

ዕዝል- 2 የአቡነ ዮሴፍ፣ ዝጊትና አቦይ ጋራ ተራራዎች ታሳቢ የማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራ የክለላ ካርታ



ዕዝል-3 የፀደቀ የቀበሌ ቃለጉባኤ (ናሙና ቀበሌ፡ ሐዋርያው ጴጥሮስ)



በሞጣ ጎጃም ዞን ጋዝጊብላ ወረዳ በ 011 ቀበሌ የአቡነ ዩሴፍ ዝጊት ማህበረሰብ አቀፍ ጥበቅ ቦታና የቀበሌውን ወሰን ክለላ ኮሚቴ ቃለ ጉባኤ

ቀን

የክለላው መነሻ ቦታ አቻለቦ

የክለላው ስራው የተጀመረበት ቀን 25/09/05

ክላው የተጀመረበት ሰዓት 4:30 ጠዋት


የስብሰባው ቦታ አስ/ር ጽ/ቤት /አዲስ ሚላም

የስብሰባው ቀን 24/09/05

የስብሰባው ሰዓት 4:00 ጠዋት

ተሳታፊዎች

		የስራ ድርሻ
1.	ፀጋየ ዘውዱ	ሊቀ-መንበር
2.	ተመኘው ለጋሌ	ም/ሊቀ-መንበር
3.	ጠርቄ ትዝዘ	አስ/ር ፀሃፊ
4.	ሃፍቴ መስፍን	መ/ድርሻ
5.	ጌጀነኝ አዲሴ	ፀሃ
6.	አስናቁ ተዴገ	ሴ/ጉዳይ
7.	ሠውነ ቤተወይ	ኅ/ጋሊዝግ
8.	አበራ ደስኝ	ሪ/መ/ር
9.	መሠረት ቤተወይ	ጤና አጠባበቅ ተጠ
10.	አሠፋ ለገዘ	ግጭርና ተጠ
11.	አወሃር ሄ ሴ	ዋና ጸሐ-ገንዘ
12.	መ/ተ አለዙ ዴስገይ	መሪወተ ሃብቴ /አስተዳ
13.	አስቻለ ሊገይ	ወ/ፍ/ክት /አስተዳ
14.		
15.		
16.		
17.		
18.		
19.		




ተበሊ አስተዳደር በኩር የአቤንዩሲና ዝኒት ማህበረሰብ አቀፍ ጥብቅ የክለላ
ቦታ ወሰን ለመከለልና ለማጽደቅ በጥብቅ የክለላ ቦታው ውስጥ የሚገኙትን የብዝሃ ህይወት ሃብቶች
ለመጠበቅ ጤናማ ስርዓተ -ምህዳር ለመፍጠር ዘለቂታ ባለው መንገድ ለመንከባከብ ፡ቱሪዝም ሊገኝ
ከሚችለው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሚታና የሥራ እድል ከመፍጠር አንጻር ጥብቅ የማህበረሰብ አቀፍ ቦታ
ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑን ሰብሳቢው ሰፋ ያለ ማብራሪያ በመስጠት ከገለጹ በኃላ
በተሰብሳቢዎች ተጨማሪ አስተያየት ተሰጥቶና ውይይት ተካሂዶ ጥብቅ ቦታው መከለል እንዳለበት
በመተማመን የወሰን ከላይ እሚቴው ያለምንም ልዩነት የሚከተለውን የውሳኔ ሃሳብ አስተላልፏል፡፡

1. የጥብቅ ቦታው ወሰን ከተበለ ---ለአተኮለሽ--- አቅጣጫ
ዝመነሳት ከለገው እቅለር /ዘሀይ/ ገሪከወርቅአስ ወመጨረሻ ደረስ
የጂፒኤስ ኮርዲኔቶን ጋር ለመሆን እህው ተመሬቶ ተሠርቷል፡፡
ከእሁኑ አካባቢ ይዋሰኖ የተከለለውን ለልንገንጠፍ ለማስጠት
ጠባቂ /ዘሀሬ/ ለመቀመር ወ አጠባት ይኖርብናል፡፡

2. ይህ የቀበሌው ጥብቅ ወሰን ከለላ ቃለ ጉባኤ ከተወሰዱት የጅፒኤስ ኮርዲኔቶች ጋር ተያይዞ
ለጋዝጊብላ ወረዳ አስተዳደር፣ ለአካባቢ ጥበቃ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት ለቀበሌው
አስተዳደርና ለአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ባህል ፡ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ በቀበሌው
ማህተም ተረጋግጦ አንዳንድ ኮፒ እንዲደርስና እንዲጸድቅ ባልተለያየ ድምጽ ተስማምተን በ-----
ጳ/09/05 ቀን ከቀኑ በ---10:00--- ሰዓት የደንበር ክለላውንና
የሪፖርት ስራ አጠቃለናል፡፡

	የኮሚቴው አባላት ስም	ፊርማ
1.	ለመለታ አባሌ ዴሳለዴ	
2.	አለለ ጌለመ	
3.	ቴሻመለ አለባው	
4.	ዴቄሬው ጌዘዘ	
5.	ሻርሃኑ ዴሞሌ	
6.	ተመኘው ለጋሌ	
7.		
8.		
9.		
10.		
11.		
12.		
13.		
14.		
15.		
16.		
17.		
18.		
19.		

ዕዝል-4 የጸደቀ የወረዳ ቃለ ጉባኤ (ናሙና ወረዳ: ጋዘጊብላ)



አጀንዳ

በ 011 ተበለ አስተዳደር በዙል አቡነየሴፍ ዝኒት ማህበረሰብ አቶፍ ጥብቅ የክለላ ቦታ ወሰን ለመከለልና ለማጽደቅ በጥብ የክለላ ቦታው ውስጥ የሚገኙትን የብዝሃ ሕይወት ሃብቶች በመጠበቅ ጤናማ ስርአተ ምህዳር ለመፍጠር ዘለቂታ ባለው መንገድ ለመንከባከብ ከቱሪዝም ሊገኝ ከሚችለው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታና የስራ እድል ከመፍጠር አንጻር ጥብቅ የማህበረሰብ ቦታ ያለው አስተዋጽ ከፍተና መሆኑን ሰብሳቢው ሰፋ ያለ ማብራሪያ በመስጠት ከገለጹ ቡኋላ በተሰብሳቢዎች ተጨማሪ አስተያየት ተሰቶና ውይይት ተካሂዶ ጥብቅ ቦታው መከለል እንዳለበት በ መተማመን ከቀበሌ የመጣውን የክለላ ቃለ-ጉባኤ የወረዳው አመራር ኮሚቴ ያለምንም ልዩነት የወሰነ ሲሆን

1. የጥብቅ ቦታው ወሰን በስተ ምስራቅ አቅጣጫ በመነሳት ከክለላው አቅሊቦ ዙሪያ በመጀመር እስከመጨረሻ ድረስ የጽ/ቤቱ ባለሙያዎች የጅኒኤስ ኮርዲቶች እና የቀበሌ ኮሚቴዎች ጋር በመሆን ስራው ተሰርቶ በመጣው መሰረት ካሁን ሰዓት ጀምሮ የተከለለውን ለመንከባከብና ለማስጠበቅ ጠባቂ(ዘበኛ) ለመቅጠርና ለማስጠበቅ ተስማምተናል
2. ይህ የወረዳ ጥብቅ ወሰን ክለላ ቃለ-ጉባኤ ከተወሰዱት የጅኒኤስ ኮርዲኔቶች ጋር ተያይዞ ለጋ/ወ/አስ/ር ለአካባቢ ጥበቃ መሬት አስ/ር ጽ/ቤት ለቀበሌ አስ/ር ጽ/ቤት ለአ/ብ/ክ/መ/ባ/ቱ/ፓ/ል/ቢሮ ለላለበላ ፍራንክ ፊርት ቅ/ጽ/ቤት በወረዳው ማህተም ተረጋግጦ አንዳንድ ኮፒ እንዲደርስ ባልተለየ ድምጽ ተስማምተን በ20/01/06ቀን በ -10:00 ሰዓት የደንበር ክለላውን አጽድቀናል

የኮሚቴ አባላት ስም ፊርማ

1. አቶ ፋንታው ፈጠነ
2. ″ ተክሉ አጣናቱ
3. ″ አባተ ማሞር
4. ንጋ ንጉስ
5. አየለ ሀብቴ
6. ደመቀ ጌሁን
7. ወንዳ ኃ
8. ዓለንታሁኑ ተክሉ
9. ወ/ሮ አጎ
10. ቆንጂ እንሰሳው
11. እጅገሰሁ ይገንዳ
12. እንዳው ሁጠኝ
13. ሄዋኮ መዐሪሻ
14. አባቱ ሄዋኮ
15. ምህረቴ ሙላ
16.